የሥራ ዝርዝር መግለጫ ቅጽ I አጠቃላይ መግለጫ		
የመስሪያ ቤቱ ስም	የሥራ መደቡ መጠሪያ	የሥራ ዘርፍ/የሥራ ሂደት
ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር	ቤተሰብ ጤና ፕሮፌሽናል I	ህብረተሰብ ጤና
	በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር.ቢሮ ብቻ የሚሞላ	
የቅርብ ኃላፊ የሥራ መደብ/ተጠሪነት	የሥራው ደረጃ	የሥራው ኮድ
	XI	
መስሪያ ቤቱ የሚገኝበት ቦታ		
በየደረጃው ባሉ ጤና ተቋማት		

II. የሥራ መደቡ ዋና ዓላማ፣ከሥራ መደቡ የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት

2.1. የሥራ መደቡ ዓላማ፡-

- በፈውስ ሕክምና አገልግሎት ለሕሙማን በምርመራና ሕክምና በማድረግ፣ በተሀድሶ ሕክምና ለአካላዊ ጉዳተኞችና ህሙማን ድጋፍና ክብካቤ በማድረግ፣ በመከላከል ሕክምና ጤናን በማጎልበት እና በሽታን በመከላከል በበሽታ የተጠቁ ህሙማንን እና የድንገተኛ አደጋ ጉዳተኞች ስቅይ መቀነስ፣ ወደ ጤናማ ኑሮአቸው መለሰስ፣ ሞትና አካል ጉዳትን በመቀነስ፣ ንቃተ ጤና በማበልፀግ፣ የበሽታን ስርጭት በመከላከል የሕብረተሰቡን ጤና ማሻሻል ነው።

2.2. ከሥራ መደቡ የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት

ውጤት **1**፡ በፈውስ ሕክምና አገልግሎት ለሕሙማን ምርመራና ሕክምና ማድረግ

- በአጣዳፊና አዝጋሚ በሽታ የተያዙ ህሙማን ይጎበኛል፣ የተለያዩ የምርመራ ስልቶችን በመጠቀም ስለሕመሙ ሁኔታ ሙሉ ቃል ይቀበላል (history taking)፣ የሰውነት አሰራር ወሳኝ ምልክቶች ይለካል (measure vital sign)፣ ሙሉ የሰውነት አካላት ምርመራ (physical examination) ያደርጋል፣
- የህሙማን የምርመራና ህክምና መረጃ ይተነትናል፤ ተጨማሪ የላቦራቶሪ ምርመራ እንዲደረግ ያዛል፣ ቀለል ያሉ የምርመራ ናሙናዎች ይወስዳል፣ ከህመምተኛው ሁኔታ በመነሳትና በተገኙ የምርመራ ውጤቶን መሰረት በማድረግ የሕመምተኛውን የበሽታ ሁኔታ ይለያል፣
- አስቸኳይ የሕክምና ዕርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ይለያል፣ ህክምና ይሰጣል፣ ከአቅም በላይ የሆነ የጤና ችግር ያማክራል፣ ለከፍተኛ ምርመራና ሕክምና ከፍ ወደአለ ጤና ተቋም ያስተላልፋል፣
- ለሕሙማን በመርፌ ወይም በአፍ የሚሰጡ መድሃኒቶችን ያዛል፣ የህመሙን ሁኔታ ይከታተላል እንደአስፈላጊነቱ የህመም ደረጃውን እያጠናና እያማከረ መድሀኒት ይለውጣል፣ በተከታታይም ለህሙሙ ቤት ለቤት የጤና ክብካቤ ያደርጋል፣
- ለሕሙማን በደም ስር የሚሰጡ የሰውነት መተኪያ ፈሳሽና ንጥረ ነገር ይሰጣል፣ በቤት ውስጥ ሊደረግ ስለሚገባ የጤና ክብካቤ ለህመምተኛውና ለቤተሰቡ ትምህርትና ስልጠና ይሰጣል፣
- የህክምና አሰጣጥ ጋር ተያይዞ ለሚደርሱ ድንገተኛ ጉዳትና ሕመም ሆነ ህክምናው ያስከተለውን ጎናዊ ጉዳትን ላይ የድንገተኛ ሕክምና ዕርዳታ ይሰጣል፣ በጉዳተኛ ማስተላለፍ ላይ ከጤና ጣቢያና ከሆስፒታል ትሪያጅ ተቀናጅቶ ይሰራል፣

ውጤት **2**፡ በተሀድሶ ሕክምና ለአካላዊ ጉዳተኞችና ህሙማን ድጋፍና ክብካቤ ማድረግ